# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከሠራው በኋላ




**ጸሐፊው**: Edward Hughes
**ምሣሌ አቅራቢው**: Byron Unger; Lazarus
**የተተረጎመው**: Zemendale Translation Service
**ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው)**: Bob Davies; Tammy S.



ታሪክ 1 ከ 60 ዎቹ መሃከል

**www.M1914.org**

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


**አማርኛ**

Amharic

ማንፈጠረን መጽሐፍ ቅዱስ ወይም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው የዞው ዛር ከብዙ ዘመናት በፊት እንዲተፈጠረና በመጀመሪያ የተፈጠረው ሰው አዳም ተምሎ እንዳተሰየመ ይናገራል። እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር አበጀው።



1

እግዚአብሔር የህይወትን እስትንፋስ በአዳም ውስጥ እፍ ባበት ጊዜ ህያው ሰው ሆነ። እሱም ራሱን እጅግ በተዋበ ኤደን በሚበልበት ገነት ውስጥ አገኘው።



2

እግዚአብሔር አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ምድርንና ሞላዋን በሙሉ እንደፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።



3

እግዚአብሔር ደረጃ በደረጃ ተራራዎችን፣ ሜዳዎችን፣ አበቦችን፣ ትላልቅ ዛፎችን፣ የሚያማምሩ አይን የሚሰጡ ወፎችን (አእዋፍትን)፣ ንቦችን፣ በባህርና በየብስ ላይ የሚገኙትን በእግር የሚራመዱና በደረት የሚሰቡትን እንስሳት ሁሉ ፈጠረ። እግዚአብሄር ሁሉንም ነገር በሠማይና በምድር፣




4

ከሁሉም ነገር በመጀመሪያ ወይም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከመፈጠሩ በፊት ምንም ዓይነት ነገር/ ፍጥረት አልነበረም ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ምንም ዓይነት ከፍታም ሆነ ዝቅታ አልነበረም፣ ትናንት ወይም ነገ በሚባል አልነበረም።
ምንም አይነት መጀመሪያ የሌለው /ያነበረው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር አደረገው።



በመጀመሪያ
እግዚአብሔር ሠማይንና
ምድርን ፈጠረ።

5

መሬትም ቅርፅ አልባ እና ባዶ ነበረች ጨለማም በጥልቁ ውስጥ ነበር። እግዚአብሔር “ብርሃን ይሁን አለ” ብርሃንም ሆነ።



6

ብርሃንም ሆነ። እግዚአብሔርም ብርሃን ቀን ብሎ ጨለማንም ምሽት ብሎ ጠራቸው። በመጀመሪያው ቀን ምሽትም ንጋትም ሆነ።



7

በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር በውሆች መሃከል ጠፈር ይሁን ውሃና በውሃ መሃከል ይካፈል አለ እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ። ሦስተኛውም ቀን እግዚአብሔር እንደህ አለ “የብስም ይሁን” አለ እንደዳለውም ሆነ።



8

እግዚአብሔር ሣር፣ አበቦች ቁጥቋጦዎችና ዛፎች እንዲሆኑ
አዘዘ ሆኑም እንዳቃሉ ተፈጠሩ። ጧትም
ማታም ሆነ ሦስተኛው ቀን።



9

እግዚአብሔር ፀሐይና ጨረቃን ፈጠረ
ማንም ሊቆጥራቸው የማይችላቸው
ከዋኩብትም በሠማይ ላይ
ፈጠራቸው። ከዚያም ጧትም
ማታም ሆነ አራተኛው ቀን።



10

ቀጥሎም እግዚአብሔር
የባህር ውስጥ ፍጥረታትን፣
ዓሣዎችንና ወፎችን
ፈጠረ። በአምስተኛውም
ቀን እግዚአብሔር ህያው
ነፉ ያላቸውን በውሃ/በባህር
ውስጥ ያሉትን
የሚንቀሳቀሱትንም
ነገሮች ትልቁን ዓሣና
ትናንሽ ትላትሎችን፣
ረጃጅም እግሮች የሏቸውን
ሰጎኖች፣ እና ትናንሽ
ዲንቢጠችንም በሙሉ
በቃሉ ፈጠረ።



11

የውሃውን አካል
ክንዲሞሉት የተለያዩ የዓሣ
ዓይነቶችንና በየብስና በባህር
በሰማይ ላይ ክንዲበረሩ
ውበት የተላበሱ ወፎችን
ፈጠረ። አምስተኛው
ቀን ምሽትም
ንጋትም ሆነ።



12

ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረ “ምድርም ህያው
የሆኑ ፍጥረታትን ታምጣ የተለያዩ እንሰሳት ልዩ ልዩ ተባዮች፣”
እና በደረታቸው የሚሳቡ የምድር ፍጥረታት ሁሉ ተፈጠሩ
ህያውም ሆኑ። ምድርን የሚያናወጡ ግዙፍ ዝሆኖች ጉማሬዎችና
ሌሎም እንሰሳት ተፈጠሩ። አታላዮቹ ጦጣዎችና አስፈሪዎቹ
አዞዎች፣ አስፈሪዎቹ ትላትሎች፣ ረዳጅሞቹ ቀጭኔዎች እና
ሁሉም የእንሰሳት ዓይነቶች በዚህ እለት በእግዚአብሔር
ተፈጠሩ። ንጋትም ምሽትም ሆነ አምስተኛው ቀን።



13

እግዚአብሔር ሌላም ተጨማሪ ነገር በስድስተኛው ቀን ፈጥሯል።
ይህም ፍጥረት በጣ ልዩ ነው ለሠው ልጅ አሁን ሁሉም ነገር
ዝግጁ ነው። በየመልኩ የሚያፈልገው የምግብ ዓይነትና
እዲያገለግሉት እንሰሳት ተፈጥረውለታል። እግዚአብሔር
እንዲህ አለ “ሰውን እንደመልካችን
በምሣሌያች እንፈጥ እሱም በምድር
ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ
ይገዛ” ስለዚህ እግዚአብሔር
ሰው በራሱ መልክ
እንደምሣሌው
ፈጠረው።



14

እግዚአብሔርም
አዳምን አለው "ከኤደን
ገነት ውስጥ መብላት
የምትፈልገውን ሁሉ
ብላ ነገር ግን ክፉና
መልካምን ከምታሳዩህ
ዛፍ ፍሬን ፈጽሞ
እንዳትበላ አለው።
ከተከለከለው ዛፍ ግን
ፍሬን ከበላህ ትሞ
ታለለህ አለው።"



15

እግዚአብሔርም "ሰው ብቻው ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም
ስለዚህ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት አለ።" እግዚአብሔር
ሁሉን አእዋፍትና አውሬዎችን ወደ አዳም
አመጣቸው አዳም ለሁሉም ስም አወጣላቸው።
ነገር ግን ከሁሉም ወፎችና አውሬዎች
መሃከል የሚመቸው አንድም አልነበረም።



16

እግዚአብሔርም
በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ
ጣለበት። ከሰውም አንድ የጎድን
እንት አወጣበትና ሴት አድርጎ
ካበጃት በኋላ ለአዳም ሰጣት።
የሠራትንም ሴት የምትመች
ረዳት አድርጎ ለአዳም
ሰጠው።



17

እግዚአብሔርም በስድስት ቀናት ውስጥ ሁንም ነገር
ፈጠረ። እግዚአብሔርም ሰባተተኛውን ቀን ቀድሶት
የእረፍት ቀንም አደረገው። በኤደን ገነት ውስጥ
አዳምና ሔዋን ፍጽም መልካምና ምቹ የሆነ
ኑሮ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ይኖሩ ነበር።
እግዚአብሔርም ጌታቸው ሆኖ የሚያዘጋጅና
የቅርብ ጓደኛቸው ነበር።



18

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከሠራው በኋላ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1-2

"የቃልህ ፍቺ ያበራል."
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16